


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## ፍቅራችን በማወቅና በማስተዋል ይሁን

**በቃል የሚጠና፦ 1ኛ ጴጥ. 3፥8**

***"ፍቅራችሁ ዕውቀትና ማስተዋል የሞላበት ሆኖ እያደገ እንዲሄድ እጸልያለሁ" (ፊልጵ1፥9)።***

### 1 ፍቅር ድንበር ወይንም ወሰን የለውም

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ምዕመናን *ፍቅራቸው በማወቅና በማስተዋል* ተሞልቶ እንዲያድግ የሚጸልይላቸው መሆኑን ይገልጽላቸዋል። በመካከላቸው በወቅቱ ይታይ የነበረው ፍቅር ብቻ ሳይሆን፥ የፍቅር ጠላት የሆኑት ክፉ ነገሮች ይኸውም፥ *ክርክር፥ ጥላቻ፥ ቅንአት፥ ምቀኝነት* እንደነበረ ግልጽ ነው። በዚህ ምክንያት ነው ጳውሎስ ከማንኛውም ነገር የበለጠ ፍቅራቸው እንዲያድግ የሚጸልይላቸው መሆኑን የገለጸላቸው። ይህን ያለበት ምክንያት የክርስትና ሕይወት የተመሠረተው *በፍቅር* ላይ በመሆኑ ነው። የክርስቶስ መንግሥት መመሪያው፥ እንዲሁም ሕጉ ሌላ ነገር ሳይሆን "ፍቅር" ነው። የዚህ ፍቅር ምንጩ፥ እግዚአብሔር ነው። "በፍቅር ውስጥ የሚኖር፥ በእግዚአብሔር ውስጥ ይኖራል፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ውስጥ ይኖራል።" ሐዋርያው ዮሐንስ *"እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል"* አለ (1 ዮሐ. 4፥16)። ቅድስና፥ መታዘዝ፥ እንዲሁም የሕግ መደምደሚያውና ምንጩ ፍቅር ነው። ወደ ፍጹም ሙላት ሊያደርሰን የሚችለውም ሌላ ኃይል ሳይሆን "ፍቅር" ነው። እኔና እናንተ ባለን ኃይልና ጉልበት ሁሉ ማፍቀር ስላለብን፥ ፍቅር ስፋቱ ከዚህ፥ እስከዚህ ድረስ መሆን አለበት ማለት ያቅተናል። ፍቅር ድንበር የለውም። ክርስቲያንን የሚገዛው "ሕግ" ሳይሆን ፍቅር ነው። ሁሉን የምናደርገው፥ በሕግ ተገደን ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር ግድ ስለሚለን ብቻ ነው።

### 2 ፍቅራችን በማወቅ የተሞላ ይሁን

ጳውሎስ *"ፍቅራችሁ ዕውቀትና ማስተዋል የሞላበት እንዲሆን እጸልያለሁ"* ሲል፥ ፍቅራችን በድንቁርና የተሞላ ሳይሆን በማወቅና በማስተዋል መሆን እንዳለበት ሲገልጽ ነው። "ዕውቀት" ሲል፥ በጽንሰ ሃሳብ *(theory)* የተገለጸውን መረዳት ብቻ ሳይሆን፥ ተግባራዊ የሆነውንም ዕውቀት ይጨምራል። እንዲሁም ፍቅር አንድ ደረጃ ላይ ደርሶ የሚቆም ሳይሆን፥ ሁልጊዜ የሚያድግ እንደሆነ እናውቃለን። እኔና እናንተ፥ በሕይወት መኖሩንና መፈጠሩን የማናውቀውን ማንኛውንም ሰው መውደድ አንችልም። የምንወደው፥ የምናውቀውን ብቻ ነው። ሳንተዋወቅ እኔና እናንተ እርስ በርሳችን መዋደድ አንችልም። ልክ እንደዚሁ የምንወደው ወንጌል፥ የምናውቀውን እንጂ የማናውቀውን አይደለም። አዳኛችንን የበለጠ እያወቅነው ስንመጣ፥ በጣም እየወደድነው እንመጣለን። አንዳንዶች እንደሚሉት *"ፍቅር ዕውር"* አይደለም። የምንወደው ያየነውና የምናውቀውን እንጂ፥ የማናውቀውን አንወድም። በመንፈሳዊ ሕይወት ዕውቀት የሌለበት ፍቅር፥ ክርስቲያኖችን ወደ ስህተት፥ ወደተወላገደ እምነት፥ ሚዛናዊ ወዳልሆነ ነገር፥ ይከታል። በማስተዋል ልጁን መውደድ የማይችል አባት፥ "ልጄን እወዳለሁ" በማለት እያጨማለቀ በማሳደግ ልጁን ገደል ውስጥ የሚከት አባት እንዳለ ግልጽ ነው። ስለዚህ፥ በፍቅራችን ውስጥ ዕውቀት ካልተጨመረበት፥ ጊዜአችንንና ጉልበታችንን ያለአግባብ እንዲባክን እናደርጋለን። ፍቅራችን በዕውቀት የተሞላ ከሆነ፥ ከብዙ ስህተት እንድናለን።

### 3 ፍቅራችን በማስተዋል የተሞላ ይሁን

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች የሚጸልየው ፍቅራቸው በዕውቀት ብቻ ሳይሆን፥ *በማስተዋልም* የተሞላ እንዲሆን ጭምር ነው። *"ማስተዋል"* ከዕውቀት በላይ ነው። *ማስተዋል የጎደለው ዕውቀት፥ ዋጋ የለውም።* ብዙ ዕውቀት ያላቸው፥ ማስተዋል ግን የጎደላቸው ብዙ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። በሀሰተኛ ትምህርት ተደናቅፈው የወደቁ፥ ብዙዎችን ያሳቱና አሁንም በማሳት ላይ ያሉት፥ አብዛኛዎቹ ለክርስቶስ ፍቅር

የሌላቸው አይደሉም። "ክርስቶስን በጣም እንወዳለን" የሚሉ ናቸው። ይሁን እንጂ፥ ፍቅራቸው በማወቅና በማስተዋል ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ፥ በቀላሉ በእንግዳ ትምህርት ይሳባሉ። ማስተዋል ስለሌላቸው የሰጧቸውን ሁሉ ዝም ብለው ይቀበላሉ፤ ያቀመሷቸውን ሁሉ ይቀምሳሉ፤ ያዋጧቸውን ሁሉ ይውጣሉ። ጠላታችን ሰይጣን ሥራውን በተቀላጠፈ መንገድ መሥራት የሚችለው፥ የክርስቲያኖችን አዕምሮ በመቆለፍ፥ በትክክሉ እንዳያስቡ በማድረግ ነው።


## 4 ከዚህ ክፍል የምንማረው ጠቃሚ ትምህርት

**ሀ** *አለማወቅ በረከት አይደለም፥ ድንቁርና፥ ወይንም አለ* ማስተዋል በረከት የሚመስላቸው የዘመኑ ክርስቲያኖች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። ስንፍናቸውን ለመሸፈን፥ በማወቅ፥ በማስተዋል የሚመላለሱትን ክርስቲያኖች ሲተቹ ይሰማሉ። አንዳንድ የዘመኑ ክርስቲያኖች፥ ከእግዚአብሔር ጋር ቅርበት አለን የሚሉ፥ ዕውቀትንና ማስተዋልን ሲንቁና ሲያጥላሉ ይሰማሉ። እንደነዚህን ዓይነቶቹን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላቸዋል *"እናንተ ሞኞች! እስከ መቼ ሞኝነትን ትመርጣላችሁ፥ በዕውቀትስ ላይ በማፌዝ ደስ የሚላችሁ እስከ መቼ ነው? እስከ መቼ ዕውቀትን ትጠላላችሁ?"* ይላቸዋል (ምሳሌ 1፥22)። ዕውቀትና ማስተዋል ምንጩ ከየት እንደሆነ፥ እንዲሁም ጥቅሙን የእግዚአብሔር ቃል ሲገልጽ እንዲህ ይላል። *"ጥበብን ጥራት፤ ማስተዋልንም ወደ አንተ አቅርባት። ብር ወይም የተሰወረ ሀብት ለማግኘት ጥረት የምታደርገውን ያህል ተግተህ ጥበብን ፈልጋት። ይህን ሁሉ ብታደርግ እግዚአብሔርን መፍራት ምን እንደሆነ ማስተዋል ትችላለህ፤ የእግዚአብሔርንም ነገር ጠንቅቀህ ለመማር ትበቃለህ። ጥበብን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው፤ ዎቀትና ማስተዋልም የሚገኙት ከእርሱ ዘንድ ነው" ይላል (ምሳሌ 2፥3-6)።* ትምህርትንና ዕውቀትን ስለሚጠሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ይናገራል። *"ትምህርት የማይወድ ሰው ድኽነትና ውረደት ይገጥመዋል"* (ምሳሌ 13፥18)። *"ማስተዋል የጎደላቸው ሰዎች ሁል ጊዜ ትክክል የሆኑ ይመስላቸዋል፤ ጠቢባን ግን መልካም ምክርን ይቀበላሉ"* (ምሳሌ 12፥15) ይላል።

**ለ** *ክርስቲያን በጎ የሆነውን ነገር ማየትና ማስተዋል ይችላል።* መልካም የሆነውን መርምሮና መርጦ የመያዝ ችሎታ አለው። የማይወደደውን እንዳይወድ፥ የማይመረጠውን እንዳይመርጥ፥ በተሳሳተ ነገር ተጠላልፎ እንዳይወድቅ በማስተዋል ይራመዳል። 1ኛ ተሰ. 5፥21 ላይ *"ሁሉን ነገር ፈትኑ፥ መልካም የሆነውን ያዙ"* የሚለውን እግዚአብሔር የሰጠውን መመሪያ ቃል አይንቅም።

**ሐ** *በማስተዋል የሚራመድ ክርስቲያን እውነትን በሚመስል ነጥብ ላይ፥ ሚዛኑን አይለቅም።* በቅርቡ አንድ የሚያሳዝን ታሪክ ሰማሁ። እንደምታውቁት ዘመናችን ከእግዚአብሔር ሰማን፥ እግዚአብሔርን በሥጋዊ ዓይኔ አየሁት፥ ልዩ መገለጥ ተሰጥቶኛል የሚሉ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች የበዙበት ዘመን ነው። ሕዝቡ ሞቅ ያለ ነገር የሚወድ በመሆኑ፥ የሕዝቡን ፍላጎት በማወቅ ሳይበስል፥ እንዲሁ ሞቅ ያለውን ነገር ይሰጡታል። ከነዚህ መካከል አንዱ፥ ከክርስቶስ ጋር በጣም የተቀራረበ ግንኙነት እንዳለው፥ ምን ያህል የተቀባ መሆኑን፥ ለእግዚአብሔር በጣም ቅርብ መሆኑን ምዕመኑ ሰምቶ እንዲያደንቀው፥ "ለምንድነው ሰይጣንን የምትፈሩት? በሌለበት ዝም ብላችሁ ሰይጣንን የምትገስጹት ለምንድነው? መኖሩንም በበኩሌ እጠራጠራለሁ" አላቸው። ሰይጣን ይህን ዓይነቱን ስብከትና ሰባኪ በጣም ይወዳል። ምክንያቱም ከፍተኛ ጥፋት ሊያደርስ የሚችለው፥ "ሰይጣን የለም" ብለው ችላ ሲሉት እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። ማስተዋል የጎደላቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን ዓይነት ጥሬ ስብከት ሲሰሙ፥ "እውነትም ሰይጣን የለም" በማለት ተዝናንተው መኖር ይጀምሩና ሳያውቁት ከጠላት ካምፕ ዘለው በመግባት እጃቸውን ለጠላት ይሰጣሉ። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ምዕመናን *"ፍቅራችሁ ዕውቀትና ማስተዋል የሞላበት ሆኖ እያደገ እንዲሄድ እጸልያለሁ"* እንዳላቸው፥ ዛሬም የእኔና የእናንተም ጸሎት ይሄን ዓይነት እንዲሆን ነው።

**የመዳንንም ራስ ቁር**



**የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።**

(ኤፌሶን 6፥17)




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

1. ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ምዕመናን ፍቅራችሁ ምን ዓይነት ይሁን ብሎ ይመክራል?

2. በፍቅር ውስጥ የሚኖር ሰው እንዴት ዓይነት ሰው ነው? (1 ዮሐ. 4፥16)

3. ጳውሎስ ፍቅራችሁ "በዕውቀት የተሞላ ይሁን" ሲል ምን ማለቱ ነው?

4. ፍቅራችሁ "በማስተዋል የተሞላ ይሁን" ሲልስ ምን ማለቱ ነው?

5. ማስተዋል የጎደለው "ዕውቀት" ጥቅሙ ምንድነው?

6. ፍቅራቸው በዕውቀትና በማስተዋል ያልተሞላ አማኞች ለምን ዓይነት ሁኔታዎች ይጋለጣሉ?

7. ዕውቀትን ስለሚንቁ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? (ምሳሌ 13፥18)

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...


1. ሐዋርያው ዮሐንስ *"እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል"* አለ (1 ዮሐ. 4፥16)። ይህ ቃል በግል ሕይወትህ/ሕይወትሽ ምን ያህል እውነትነት አለው?

2. ክርክር፥ ጥላቻ፥ ቅንአት፥ ምቀኝነት በልብህ/በልብሽ ውስጥ ምን ዓይነት ሥፍራ ይዘዋል?

3. በቂ ዕውቀት በማጣት በሕይወትህ የደረሰብህ/የደረሰብሽ ጉዳት ምንድነው?

4. ባለማስተዋልህ/ባለማስተዋልሽ የደረሰብህ/የደረሰብሽ ጉዳት ምንድነው?

5. ዕውቀትንና ማስተዋልን በሕይወትህ/በሕይወትሽ ለመጨመር ለማድረግ ያሰብከው/ያሰብሽው ምንድነው?



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

Ethiopian Outreach Ministry
P.O.Box 2241
York, PA 17405
U.S.A.
Phone/Fax: (717)846-2041
E-Mail: eomusa@aol.com
Internet Address:
www.ethiopianoutreach.com

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን
አድራሻ